ዐሊይሂ አፍዶሉ ሶላቲ ወሰላም

ከላዕላዩ ዓለም ተጋብዘው፣

በታላቁ ጂብል ታጅበው፣

ሰባተኛው ሰማይ ድረስ ወጡ፣

ሲድረተል ሙንተሃ ደረሱ፣

ጀነተል መእዋ አጠገብ ቆሙ፣

የትኛዉም የአላህ ፍጡር ካልደረሰበት ዘለቁ፣

በከብር ደርሰው ተመለሱ፣

መሬት ወረዱ፣

ከልዩና ላቅ ካለ ቦታ ነው የመጣሁት ብለው አልኮሩም፣

ልዩ ከብር ይገባኛልም አላሉም፣

እንደዉም እኔ የደሃ ልጅ ነኝ አታጥሩኝ አታጥራሩኝ አሉ፣

እኔ የአላህ ባርያ እና መልዕከተኛው እንጂ ሌላ አይደለሁም አሉ፣

ዝቅ ብለው ቤተሰባቸዉን አገለገሉ፣

ፍየል አለቡ፣ ማገዶ ሰበሩ፣

ልብስ ጫማቸዉን ሰፉ፣

ከድሆች ጋር ቁጭ ብለው በሉ፣

የቲሞችን አቀፉ፣ የደካማ ሴቶችን ብሶት ሰሙ፣

የችግረኞችን ችግር ፈቱ፣

አዎ ታላቁ ነቢይ ...

በልዩ ክብርና መስተንግዶ ወደ ሰባተኛው ሰማይ ወጡ፣

ሲወጡ ትልቅ ነበሩ፣

ሲወርዱም ክብር ጨመሩ፣

ሙሐመድ ታላቁ የአላህ መልዕከተኛ

አሕመዱ ታላቁ የእዝነት ነቢይ፣

እንዳንቱ ያለ ማንም የለም።

ዐሊይሂ አፍዶሉ ሶላቲ ወሰላም።

ተውሒድን እናመሰግን ..

ስለ እስልምና ሁሌም አላህን ሱ.ወ. እናመሰግናለን። ብዙዎች ያልታደሉት ሃይማኖት ነው:: ስለ ተውሒድም ሁሌም ለርሱ ሸከር እናደርሳለን:: ተውሒድን ባናውቅ ኖሮ በስንቱ ኮተት እንረበሽ ነበር። በስንቱ አልባሌ አመለካከት እንሸወድ ነበር። ለስንቱ ዝባዝንኬ እንሰግድ እናጎበድድ ነበር:: ተውሒድ ባልማር ኖሮ የዉስጥ እጇን ባሳከከኝ ቁጥር ሪዝቅ ሊመጣ ነው ብዬ ሰፍ አል ነበር እኮ። ማታ ላይ እጅህን ካሳከከህ እጅህን ታጥበህ ተኛ:: ሌላ ትርጉም የለዉም::

ባትችል ባትችል ...

ቀንህ ደርሶ ይህችን ምድር እስከትሠናበት ድረስ በየቀኑ የምታዘወትረው የሆነ ኸይር ሥራ አትጣ:: ከቁርአንም ከዚከርም ትንሽም ብትሆን ቀምሰህ ዋል:: የአል-በቀራን ምዕራፍ ማንበብ ባትችል ቁል አዑዙዎችን እና ቁል ሁወሏሁ አሐድን አንብበህ ዋል። ይህን ቢያቅትህ አየት አልኩርሲይን ማንበብ አትርሳ። ቀኑን ሙሉ ከቁርአን ከመገናኘት ብትሰንፍ የጠዋት እና የማታ አዝካሮችን አትርሳ። ካልሆነም ከሶላት በኋላ ባሉ ዚከሮችና ዱዓዎች ላይ በርታ። ለዚህም ባትታደል ኢስቲግፋርን ለምላስህ አስለምድ። ይህንንም ሳታደርግ የዋልክ እንደሆነ የመኝታህ ሰዓት ዚከሮችን አስታውስ። ድከመት ማለት በቀን አንድ ጊዜም ቢሆን ወደ አላህ ሳይመለሱ፣ አላህን ሳያወሱ መዋል ነው። አላህ ያበርታን፣ አላህ ያስታውሰን። ቲስበሑ ዐላ ኸይር ...

ከሙአሚን ባህሪ ...

ሳታስተዉል በሆነ ሰው ላይ የሆነ ጥፋት አጥፍተህ "ባለማስተዋል ያደረግኩት ነገር ነዉና ዐፍዉ በለኝ::" ብለኸው ያ ሰው ግን እንዳኮረፈና አሻፈረኝ እንዳለ ቢቀጥል ምን ታደርጋለህ? ይቅርታ ተጠይቆ ይቅር የማይል ሰሰው ሸይጧን ነው ይላሉ:: ብታጠፋበትም ባታጠፋም ሙአሚን ከሆንክ የሆነ ሰው ሲያኮርፍህ ዉስጥህ መናጋቱና ሰላም ማጣትህ ግድ ነው። ነገሩ "ጉዳዩ ነው ያኩርፍ::" ብለህ እንዲሁ በቀላሉ የምታልፈው ነገር አይደለም። ምክንያቱም አንድን የዲን ወንድም ማጣት ከባድ ነገር ነዉና። አንዳንድ ሰው ሁኔታዉን ስናይ ሰዉን በማኩረፍ የሚደሰት ይመስላል:: ሌላው ደግሞ ሰዉን አስኮረፍኩ ብሎ ሰላም ያጣል። በሁለቱ ሰዎች መካከል የኢማንና የሥነምግባር ልዩነቱ ሰፊ ነው:: አላህ ሰዎችን በየመልከና የተለያየ ባህሪ ፈጥሯል። መልክ ባይስተካከልም ባህሪ ግን በኢማን ይቃናል። ሙአሚን ያጥፋም አያጥፋ እኔ በቃ ባህሪዬ እንዲህ ነው ብሎ በድርቅናው አይቀጥልም፣ መለስ ብሎ ራሱን ይገመግማል።

ብርሃናማው ነቢይ ..

"ምንም የምናበራው ነገር ባልነበረን በነዚያ የጨለማ ቀናት ዉስጥ የሚበራልን የመሐመድ ፊት ብቻ ነበር።" ትላለች ሞግዚታቸው የነበረችው ሐሊማ አስ-ሰዕዲያ። እርሣቸው የፍጥረተ ዓለሙ ብርሃን ናቸው። አካላቸው ብርሃን ነበር። በአስተምህሯቸዉም ዓለምን ከዳር እስከዳር አብርተዋል። ሶልለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም።

ነገርህን ሁሉ አደባባይ አታስጣው ..

ዘመኑ ለመታወቅ ግርግር የበዛበት ሆኗል። ብዙ ሰዎች ቤት መዋልና መሰተርን ከተዉ ሰንበትበት ብለዋል። የቤታቸዉን ሕይወት ወደ አደባባይ አውጥተው በተለይ በፎቶና በቪዲዮ በየሶሻል ሚዲያው ይገልጣሉ። የባሰባቸው ደግሞ ገመናቸዉን ጭምር በአደባባይ ያሠጣሉ። ይታወቁ እንጂ ስለሌላው ነገር ጉዳይ የለንም የሚሉ ይመስላሉ: : በርግጥ ደስታን ማወጅ መልካም ነገር ነው፤ ምስጋናም እንደሆነ አውቃለሁ። ግና በተጋነነ መልኩ ሲሆን ይጨንቃል። ካገቡ አገባሁ እወቁልኝ ብሎ ማሳወቅ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ፣ ከወለዱም እንደዚያው።

ዘመኑ ሰው ከስኬትህ ይልቅ ዉድቀትህን ለመስማት የሚያሰፈስፍበት ዘመን ነው። ብዙ ሰው ተጋቡ የሚለዉን ትልቅ ዜና ትቶ ተፋቱ የሚለዉን ዜና ለመስማት ወደፊት ሮጦ ቁጭብሎ ይጠባበቃል። ወዳጄ ... ዱንያ ላይ ስትኖር ብዙ ጊዜህን ብትሰተር ነው የሚሻልህ። የሰዉን ነገር እንኳን በአደባባይ ወጥተህ ተሰትረህም አትችለዉም። ዛሬ ላይ ብዙዎች የተለያዩ አላስፈላጊ ድርጊቶችን ባደባባይ የሚፈፀሙት መነጋገሪያ ለመሆን ነው። ሰው አየህ አላየህ፣ ስለ ሰርግህ እና ድግስህ አወራ አላወራ ምን ይጠቅምሃል?። ባይሆን አላህ የሰጠህን ፀጋ ከወረኛም ከምቀኛም በመደበቅ ተንከባከብ፣ ምቀኛ ከአፍም ከዐይንም ይነጥቃል። በሀሳብ እየተለዩ፣ በፎቶ እየገነኑ አነጋጋሪ መሆንም ሆነ ቫይራል መባል ጀነት አያስገባም። ጀነት የሚያስገባው ተሻጋሪ ዒባዳ እና መልካም ሥራ ነው። ሌላው ዱንያዊ ጉዳይ ሁሉም እዚሁ ዱንያ ላይ የሚቀር ነገር ነው። ወሏሁል ሙስተዓን።

ብዙዎች ልብ ያላሉት ትግል ..

ወዳጄ ... ሕይወት በየፈርጁ ትግል ናት። ግና ብዙዎች ልብ ያላሉት አንድ ከባድ የሆነ የጂሃድ (ትግል) ዓይነት አለ። እሱም ደስታን ለማግኘት ደስተኛ እንደሆኑም ለመዘውተር የሚደረግ መታገል ነው። አዎ ደስታን ለማግኘት ራሱ ከባድ ትግል ይፈልጋል።

የትካዜና ርሃብ ጥቅም

አላህ አንድ ባርያዉን የወደደው እንደሆነ እይታዉን ያበራለታል፤ እይታን ማብራት ስንል እውነትንና መንገዱን ሁሉ ማወቅ ነው። ራስን ማንበብ መቻል ነው። ዑለሞች እንደተናገሩት እይታን ከሚያበሩ ነገሮች መካከል ርሃብና ትካዜ ይጠቀሳሉ። ሆድ ባዶ ሲሆን እንዲሁም ትካዜና ሐዘን ሲገባው ሰዉየው እይታው ይበራል፤ የያንዳንዱን ነገር ምንነት ያውቃል፤ ራሱን ያውቃል፣ የቀልቡን ሁኔታ ያውቃል፣ የባልደረቦቹንም የቤተሰቦቹን እንዲሁም የቤተሰቦቹን ተጨባጭ ያውቃል፣ የዱንያን ምንነት ያውቃል። የተራበ ሰው ቀልቡ ይለሰልሳል፣ እዝነትን ይላበሳል፣ ርህራሄን ይጎናፀፋል። ትካዜ ራስን ማያ መስታወት ነው። ራስን ያስመለከታል። ሰው ወደ ዉስጡ ይመለከትና ቀልቡ ምን ላይ እንደደረሠች ያውቃል፤ በትንሽ ጊዜ ዉስጥ ብዙ ነገሮችን ይገነዘባል። ሩሑ ሥራ አትፈታም፣ ወደ ሰማይ ትመጥቅና ከአላህ ጋር የበለጠ ትተሳሰራለች፣ ርሃብም ሆነ ሐዘን ወደ አንድ የአላህ ባርያ ዉስጥ አይገቡም ልቦናዉን ያበሩለት የነገሮችን እውነታ የገለጡለት ቢሆን እንጂ። ርሃብን አትጥሉ፤ ትካዜንም አትፍሩ። (ከኢማም ኢብኑ ከሢር ሀሳብ የተወሰደ)

አንድ ጠቢብ እንደተናገሩት ...

' ከሰው ልጅ ሁሉ ደካማው ሚስጢሩን መደበቅ የማይችለው ነው፤ ጠንካራው ቁጣዉን የሚቆጣጠረው ነው፤ ታጋሹ ድህነቱን የሚደብቅ ነው፤ ሀብታሙ አላህ በሠጠው ነገር የተብቃቃው ነው።

ከነፍስ ሐቆች መካከል ...

ነፍስህ ባንተ ላይ ብዙ ሐቅ አላት። ከሐቆቿ መካከል አንዱ አጠቃላይ የሆነ ሰላም ለሷ መስጠት ነው። ለነፍስህ ሰላምን ከምትሠጥበት መንገድ አንዱ የሚረብሻትን ሰው አጠገቧ እንዳይደርስ ማባረር ነው። በዚህች አጭር የዱንያ ሕይወት ላይ ዘና ብለህ የመኖር፣ ነፍስህን የማስደሰት፣ መምከር፣ ማከም፣ ማረጋጋት፣ ማበረታት፣ መኮትኮት፣ ማሳደግ፣ ማምጠቅ፣ ... ሙሉ መብት አለህ። ከዚህ ጥረትህ የሚያሰናክልህ ሰዉም ሆነ ሁኔታ ካለ መጋፈጥ፣ ማሰናበት፣ መፋታት ለነፍስህ ሰላም ዋስትና ነው። በምድራዊ ሕይወቱ አሉታዊ ነገር ብቻ የሚታየው ሰው ተረብሾ ሊረብሽህ የመጣ በሽተኛ ነው። ዱንያን ሳትኖራት እንድታልፍ ሊያደርግህ ነዉና ፈጽሞ አትጎራበተው። ሕይወትን ለማቅለል ስትለፋ ካላከበድኩ ብሎ የሚታገልህን ሰው ወዳጅህ አታድርግ። መጉቀል አሊያም መራቅ ሲቻል ከእሾህ ተጠግቶ ዘላለም እያነቡ መኖር ደካማነት ነው፤ ነፍስንም መበደል ነው የሚሆነው።

እንፈግግ

የፍቅሂ ነገር ...

በሻፈዒያ መዝሀብ ዒባዳ ተብለው በሚታሰቡ ተግባራት ዉስጥ ሁሉ ንያን አውጥቶ መናገር የሚወደድ ተግባር ነው።

አባቱ ታላቅ ሊቅ የነበረው ኢማም አባልፊድል አልሀመዛኒ ስለ ልጅነት ሕይወቱ ሲያወጋ እንዲህ ይላል፡-

አባቴ አላህ ይዘንለትና ሊመታኝ ሲፈልግ እንዲህ ይል ነበር - " አላህ ልጆቻችንን በሥርዓት እንድናሳድግ ባዘዘው መሠረት ልጄ መጥፎ ልጅ እንዳይሆን ልቀጣው አስቤያለሁ ።"

እኔም እሱ አስኪነይትና ኒያው የተሟላ አስኪሆን ድረስ እኔ ሮጬ አመልጥ ነበር። (አል-ቢዳያ ወን-ኒሃያ)

ገልብጦ ማንበብ (ለፈጣታ)

ሶቅራጠስ እንዲህ ይላል፡-

"ልጅ ሆኜ ጠዋት ማልዶ የመነሳት ነገር አይሆንልኝም ነበር፣ እናቴ ጎበዝ ነጋዴ እንድሆን ስለምትፈልግ ይህን ባህሪዬን አትወድም ነበር:: አንድ ቀን እንዲመከረኝ ብላ ወደ መምህሬ ይዛኝ ሄደች:: መምህሬም

"ሶቅራጠስ፤ የሆነች አጭር ታሪክ እነግርሃለሁ፤ ከዚያ ምን እንደተማርክ ትነግረኛለህ :: " አለኝ::

"እሺ" አልኩት::

"ሁለት ወፎች ነበሩ:: አንደኛው በጠዋት ተነሳና ብዙ ትላትሎችን አገኘ፤ ለራሱ በላ፤ ልጆቹንም አበላ:: ሁለተኛው ደግሞ አርፍዶ ሲነሳ የሚበላዉን አላገኝም:: ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን? " አለኝ::

እኔም "ማልደው የሚነሱ ትላትሎች በወፎች እንደሚበሉ ነው::" ብዬ መለስኩ::

ዋናዉን ሀሳብህን ማግኘት አቅቶት እንዲህ ገልብጦ በማንበብ ልፋትህን መና የሚያስቀርም ብዙ ሰው አለ ለማለት ነው ያመጣሁት::

ዐሊይሂ አፍዶሉ ሶላቲ ወሰላም

ከላዕላዩ ዓለም ተጋብዘው፣

በታላቁ ጂብል ታጅበው፣

ሰባተኛው ሰማይ ድረስ ወጡ፣

ሲድረተል ሙንተሃ ደረሱ፣

ጀነተል መእዋ አጠገብ ቆሙ፣

የትኛዉም የአላህ ፍጡር ካልደረሰበት ዘለቁ፣

በከብር ደርሰው ተመለሱ፣

መሬት ወረዱ፣

ከልዩና ላቅ ካለ ቦታ ነው የመጣሁት ብለው አልኮሩም፣

ልዩ ከብር ይገባኛልም አላሉም፣

እንደዉም እኔ የደሃ ልጅ ነኝ አታጥሩኝ አታጥራሩኝ አሉ፣

እኔ የአላህ ባርያ እና መልዕከተኛው እንጂ ሌላ አይደለሁም አሉ፣

ዝቅ ብለው ቤተሰባቸዉን አገለገሉ፣

ፍየል አለቡ፣ ማገዶ ሰበሩ፣

ልብስ ጫማቸዉን ሰፉ፣

ከድሆች ጋር ቁጭ ብለው በሉ፣

የቲሞችን አቀፉ፣ የደካማ ሴቶችን ብሶት ሰሙ፣

የችግረኞችን ችግር ፈቱ፣

አዎ ታላቁ ነቢይ ...

በልዩ ከብርና መስተንግዶ ወደ ሰባተኛው ሰማይ ወጡ፣

ሲወጡ ትልቅ ነበሩ፣

ሲወርዱም ከብር ጨመሩ፣

ሙሐመድ ታላቁ የአላህ መልዕከተኛ

ኡሕመዱ ታላቁ የእዝነት ነቢይ፣

እንዳንቱ ያለ ማንም የለም።

ዐሊይሂ አፍዶሉ ሶላቲ ወሰላም።

ለምን እናነባለን ..

1- ዕውቀትን ለመጨመር እናነባለን፣
2- ጊዜያችንን በአግባቡ ለመጠቀም እናነባለን፣
3- ከድብርት ለመገላገል እናነባለን፣
4- እቤት ቁጭ ብለን ዓለምን ለመዞር እናነባለን፣
5- ለመዝናናት ብለን እንነባለን፣
6- የማስታወስ አቅማችን እንዲዳብር እናነባለን፣
7- መልካም ትዝታዎችን ለማምጣት እናነባለን፣
8- ሥራ ላለመፍታት እናነባለን፣
9- ከሥራ ፈቶቸ ለመራቅ እናነባለን፣
10- መንፈሳችን እንዲታደስ እናነባለን፣
11- ፈጣግ ለማለትና ቆዳችን ለማፍታታት እናነባለን፣
12- ለሙተከዝና ለመቆዘም እናነባለን፣
13- ከሀሳብ ለማምለጥ እናነባለን፣
14- በሰው ቦታ ሆነን ራሣችንን ለማየት እናነባለን፣
15- ተስፋን ለመሰነቅ እናነባለን፣
16- ባህሪያችንን ለማሻሻል እናነባለን፣
17- አዲስ ነገር ፍለጋ እናነባለን፣
18- የሰዉን አይታና አመለካከት ለማሰስ እናነባለን፣
19- በምናብ ለመዞር እናነባለን፣
20- የራሳችንን ታሪክ ከሌላ ሰው ለመስማት እናነባለን፣
21- ከብቸኝነት ለመውጣት እናነባለን፣
22- ለመነሳሳትና ለመበርታት እናነባለን፣
23- ስህ,ተታችንን ለማረም እናነባለን፣
24- ያነበብነዉን ለማካፈል እናነባለን፣
25- ከእንቶፈንቶ ወሬ ለመራቅ እናነባለን፣
26- ሌሎች እንዲያነቡ ለመገፋፋት እናነባለን፣
27- አዳዲስ ሰዎችንና ሀሳቦችን ለማግኘት እናነባለን፣
28- ያለንበትን ሁኔታ ለመቀየር እናነባለን፣
29- የቀደመዉንና ያለፈዉን ትውልድ ለማነፃፀር እናነባለን፣
30- ኢማናችንን ለማሳደግ እናነባለን::